# <u>ይድረስ ለብርቱዋ</u>

## ቁ.5 ከከበቡሽ አየናቸው

ብርቱዬ    ዘኢትዮጵያ!
የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ!
የጀግኖች መዘከሪያ!
የፖልለቲካ እስረኞች አርአያ!
የክላራዜስኪን አምሳያ!
የወላጆች መመኪያ!
የሴቶች መደነቂያ!
የታሪክ መፋረጂያ!
የትዕግስት ገበያ!
የእምነት፣ የፅናት መማሪያ!

> ብርቱዬ ጀግናዋ! ይህ ሁሉ ያንስሻል!
> የእግዜር ብርቱ ፍጥረት ብልሽ ይበቃሻል?
> እንደምን ባዥተሻል? እንደምንስ ከረምሺ?
> ምን ይሰማሽ ይሆን? እየነጋ ሲምሺ?!

የወያኔ ልጆች፣ ሃይማኖት የላቸው፣
ህሊና የሚባል፣ አልፈጠረባቸው፣
ጢትም ሆነ ማታ፣ ዘወትር በተንኮል፣
በበደል ላይ በደል፣ በበቀል ላይ በቀል።
በአዋጅ ላይ አዋጅ፣ በሽብር ላይ ሽብር፣
በሰበብ ላይ ሰበብ፣ በእሥር ላይ እሥር፣
ፍፃሜው ምን ይሆን፣ የዕብሪታቸው ነገር?!
ለእናትነትማ አዜብም እናት ናት፣
ግን የሃሌ ችግር፣ መች ነው የሚገባት?!
ያባትነትማ መለስም አባት ነው፣
ግን የሃሌ ችግር፣ መች ነው የሚሠማው?!

> “እባክህ ፈጣሪ፣ የብርቱካን አምላክ፣
> ልመናችን ሥማ፣ መንግሥትህ ይባረክ፣
> ከአፈ-አናብስት፣ ዳንኤልን ባርከህ፣
> ቂርቆስ እየለጣን፣ ከእቶን እንደታደግህ፣
> ሠልሥቱ ደቂቅን፣ ከእሣት እንዳዳንክ፣
> ቴዲን በምህረትህ፣ የኀበኘህ ጌታ፣
> ብርቱዬንም ባርካት፣ ማሰሪያዋን ፍታ፣”
> እያልኩ ከመጸለይ፣ ከመለመን በቀር፣
> ሌላ በምን ልርዳሽ፣ ያማል ያንች ነገር።

አንድ ጋዜጠኛ፣ እማማን አንድ ቀን፣
በዚያ በእሥር ቤቱ፣ መከራ ሠቀቀን፣
“ማነው አብሯት ያለ፣ እማማ?” ሲላቸው፣
በጣም ፈጣን ነበር፣ የእማማ መልሳቸው።
“ሌላ ማን ይኖራል፣ እሷስ ብቻዋን ናት፣
ግን ታላቁ ጌታ፣ መቼም አይለያት።”

ባለሃይማኖቱዋ፣ እኒያ ብርቱ እናትሽ፣
ይህን ሲናገሩ፣ የሰማ ወገንሽ፣
ሁሉም በያለበት፣ ተንሰፈሰፈልሽ።

አሁንም ብርቱዬ! ያንች አነጋጋሪ፣
የእማማ፣ የአባባ፣ የሃሌ ፈጣሪ፣
እሱ ያውቅልሻል፣ ለእሱ ተናገሪ፣
ከልብ ከለመኑት፣ እምነትን አፅንቶ፣
ምን ተስኖት ያውቃል? አይረሳሽም ከቶ!

ብርቱዬ ሥለአንች፣ የግፍ ግፍ መታሰር፣
በውስጥም፣ በውጪም ተጯጩኋል አገር።
ያለም መንግሥታትም፣ ሃያላኑ ሁሉ፣
ሥለአንች መበደል፣ አውቀዋል በሙሉ፣
አሜሪካኖችም፣ በደሉን ያውቁታል፣
በተደጋጋሚ ትፈታል ብለዋል፣
ግን ያለብን ችግር፣ የተወሳሰበው፣
ምዕራባዊያኑን፣ የኋሊት የሳበው፣
“ልጅን ሲሳስሙ፣ ልጅን ሲያባብሉ፣
ከነለሃጩ ነው” እንደሚባል ሁሉ፣
ከምጥ ያዋለዱት፣ ወያኔ ልጃቸው፣
“ላም እሣት ወለደች” ሥለሆነባቸው፣
ልንቀድም አልቻልንም፣ ከጊዜው ጥቅማቸው።

ያም ሆኖ ወያኔ፣ ጥጋብ ስለማይችል፣
ይኸው በየቀኑ፣ በጣም ይጋለጣል፣
በአዋጅ ላይ አዋጅ፣ እያነባበረ፣
እራሱ ሽብርን፣ አውቆ እየፈጠረ፣
ንጹሃን  ዜጎችን፣ በግፍ እያሰረ፣
የድርጅቶችን መብት እየሻረ፣
ሥለዴሞክራሲ፣ እየቀባጠረ፣
ሰብአዊ መብትን፣ ሥለሰባበረ፣
ሁሉም አውቆበታል፣ ትዕቢቱ እንደናረ!!
መልካም አስተዳደር፣ የሚባለው ነገር፣
ፈጽሞ እንደሌለ፣ በኢትዮጵያ ምድር፣
በውስጥም፣ በውጪ አውቆበታል አገር።

በተለይም አሁን፣ የምርጫው ቀን ሲደርስ፣
ተቃዋሚዎችን ማዋከብ፣ ማራከስ፣
መድረክ በመከልከል፣ እርስ በእርስ ማናከስ፣
ዙሪያውን አፍኖ፣ ቢሯቸውን ማፍረስ፣
ማበጥ፣ መንጠራራት፣ ሌላውን ማንኳሰስ፣
የዕለት ሥራው ሆኗል፣ “ዴሞክራቱ” መለስ።
ለዴሞክራሲያዊ የምርጫ ውድድር፣
በሩ መዘጋቱን፣ ባገር ዳር እስከዳር፣
ምዕራባዊያኑ፣ በቅርብ ያውቃሉ፣
የወያኔን ዕብጠት፣ ጧት ማታ ያያሉ፣
ሥራቸው ይኸው ነው፣ ምን ይጠብቃሉ?!

የጉዳዩን ይዘት፣ ያስተሳልፋሉ፣
ካፍንጫቸው ደርሷል፣ በደሉ በሙሉ።

የወያኔን ምርጫ፣ በቅረበት ሲያጠኑት፣
«ሱሪውን አውሶ፣ አትቀመጥበት፣»
ያለውን ይመስላል፣ የዱሮውን ተረት::

መቼም ባገራችን፣ አይሰማ የለ!
በናዝሬት ስብሰባ፣ ሁሉን ባካፈለ፣
ባማርኛ ቁዋንቁዋ፣ አትስሩ ተባለ::
ስብሰባው በጉልበት፣ በግፍ ተበተነ ፣
የወያኔ መንግስት፣ እንደሌለ ሆነ::
በህገ-መንግስቱ የተሰጠው መብት
ናዝሬትም ተሻረ፣ ወያኔ ለየለት::
ብልሽትሽቱ ወጣ፣ ያ የደከምሽበት፣
ከሁሉም ከሁሉም፣ ይህ ነገር ይከፋል፣
ጭፍን ዘረኝነት ፣ በጣም ይከረፋል፣
በስባሳው ኢሕአዴግ፣ ይበልጥ ተበሳብሷል::

የወያኔ መንግስት፣ አላቂ ቡትቶ፣
ለእኔ እንደሚታየኝ፣ ሁለንተናው ጎልቶ፣
ብስክስክ የሚል፣ ይመስለኛል ሳስቶ::

አራት ኪሎን እንኩዋ፣ መጠበቅ ተስኖት፣
ወይም ሲያጭበረብር፣ በተለመደው ስልት፣
ወታደር ሲሰብረው፣ የጳጳሳቱን ቤት፣
አጥፊውን ለይቶ፣ ማውጣት ከተሳነው፣
ወያኔ የት ይሆን ፣ አለሁኝ የሚለው?
በአባ ጳውሎስ ላይ፣ ይኸ ቢደርስ ኖሮ፣
አገር በታመሰ፣ ከሽብር ተቆጥሮ!!!

ብርቱዬ ጠንክሪ ፣ ዘንድሮ ማን ያውቃል፣
እንደ ዐይጥና ድመት፣ ያባላው ይሆናል::
«እግዜር ሲጠላ፣ በትር አይቆርጥም፣
ያደርጋል እንጅ፣ ነገሩ እንዳይጥም::»
እንደሚሉት ሁሉ፣ አበው ሲናገሩ፣
የእርሱን ፍርድ ማን ያውቃል? ዕፁብ ነው ምስጢሩ፣
ጉልበት ያላችሁም፣ በስፖርቱ ጠንክሩ::

ብርቱዬ ብርታትሽን ፣ ሁሉም ተረድቶታል፣
የሚሳነው የለም፣ መዲኃኒዓለም ያውቃል፣
ለሰላምታ ያህል፣ ለዛሬው ይበቃል::

(የምሳሳልሽ እህትሽ ከበቡሽ አየናቸው)